የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

# ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
# CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ምንጩ ያልታወቀ

# ሀብትን ማጋለጥ ሙስናን ለመከላከል ያለው ፋይዳ

# በሚል ለባለድርሻ አካላት ለውይይት የቀረበ ሰነድ

ጥር 2015 ዓ.ም
ሰመራ

# ይዘት

- ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ምንነት እና ፋይዳው
- የሀብት የማፍራት መብት
- ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማጋለጥ እና ሀብት ማስመለስ ዓለም ዓቀፍ ተሞክሮዎች
- ምንጩ ያልታወቀ ሀብት የህግ ማዕቀች
- ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ለማጋለጥ ሚና ያላቸው አካላት
- ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማጋለጥ ተግዳሮቶች
- በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

# ሀብት የማፍራት መብት

በ1948 እ.አ.አ የወጣው UDHR አንቀጽ 17 መሠረት ሁሉም ሰው በግል ወይም በጋራ ንብረት የማፍራት፤ የንብረት ባለቤት የመሆን እና ያለፍርድ ንብረቱን ሊነጠቅ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡

በኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ማንኛውም ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት የመሆን መብት አለው፡፡ ይህም መብት የዜጎችን መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብትን የሚያካትት ነው፡፡ ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ የሚገኝና ማንኛውን ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ተጠያቂነትን የሚያስከትል ጉዳይ ነው፡፡

# ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ምንነት እና ፋይዳው

ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማለት ከገቢ በላይ ሀብት መያዝ ሲሆን የሚያስቀጣ ወንጀልም ነው፡፡

የዓለም እና የአህጉር አቀፍ ኮንቬንሽኖች አባል ሀገራት ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን የሙስና ወንጀል አድርገው ህግ እንዲደነግጉ ያበረታታሉ፡፡

የሀብት ምዝገባ ስርዓት የጥቅም ግጭትን ለማስተዳደርና ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን ወይም አላግባብ የመበልፀግ ሂደትን ለማጋለጥ (detect illicit enrichment) ትልቅ ፋይዳ አለው (de Michele and Dassen, 2018)፡፡

# ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማፍራት በኢትዮጵያ ህግ

## ኢትዮጵያ ምንጩ ያልታወቀን ሀብት፡-

- በ1996 ዓ.ም በወጣው የተሻሻለው የወንጀል ህግ፡፡
- በተባበሩት መንግስታት ፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን አንቀፅ 20 (አዋጅ ቁ. 544/99)
- በአፍሪካ ሕብረት የሙስና መከ/መዋጊያ ኮንቬንሽን አንቀፅ 8 (በአዋጅ ቁ. 545/99)
- የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 21 ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን የሙስና ወንጀል በማድረግ የደነገገች ሲሆን ህጉም በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን ለመዋጋት እና ለመከላከል የሚረዳ ነው፡፡

# ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ዓለም አቀፍ ተሞክሮ

## ፊሊፒንስ

- ባለፉት 21 ዓመታት ውስጥ በፈርዲናንድ ማርኮስ (10ኛው ፕሬዚዳንት ከ1965-1986) የተሰረቀውን ከስዊዘርላንድ ከ1 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገንዘብ አስመልሳለች፡፡
- ግለሰቡ እስከ 10 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሀብት አላግባብ እንዳካበቱ ይገመታል፡፡
- በአብዛኛው ሀብቱን ያሸሹበት ሁኔታ የሀገሪቱን የጦር መሪያ ግዥ ውል ጋር ተያይዞ ነው፡፡ ይህንን በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ ለማቅረብ (money loundary) የፕሬዚዳንቱ ቤተሰብ ሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የግል ንግድ ድርጅቶች እንደ ሼል ኮርፖሬሽን እና ሪል ስቴቶችን ያንቀሳቅሱ ነበር፡፡ ሀብቱ የተመለሰበት አግባብ The Presidential Commission on Good Govermnet (PCGG) እና informal representation on US and Swiss to freeze the stolen assets.
- ሀገሪቱ የተመዘበረውን ሀብት ለማስመለስ 18 ዓመታት ፈጅቶባታል፤

# ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ዓለም አቀፍ ተሞክሮ…የቀጠለ

**ፔሩ**


- በ2007 በቭላዲሚር ሞንቴሲኖስ (ፕሬዚዳንት 1990-2000) የተመዘበረውን በስዊዘርላንድ፣ ካይማን ደሴቶች እና ዩናይትድ ስቴትስ ካሉ ግዛቶች ከ174 ሚሊዮን ዶላር በላይ አስመልሳለች፤
- በፕሬዚዳንቱ አስተዳደር ሀገሪቱ ከ2 ቢሊዮን በላይ የአሜሪካን ዶላር ተመዝብራለች፤
- በአብዛኛው ገንዘቡ የተመዘበረበት አግባብ ከትላልቅ የግዥ ውሎች ጋር ተያያዥነት አለው፤
- የተመዘበረው ሀብት የተመለሰበት አግባብ የፕሬዚዳንቱን ስልጣን መልቀቅ ተከትሎ ሀገሪቱ ያቋቋመችው የፍትህ ተቋማት ሪፎርም (Creation of Prosecution agencies and anti-corruption courts with innovated judicial system) ትልቅ ድርሻ ወስዷል፤

# ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ዓለም አቀፍ ተሞክሮ…የቀጠለ

## ናይጄሪያ

- በሳኒ አባቻ (ፕሬዚዳንት 1993-198) የተዘረፈ 700 ሚሊዮን ዶላር በስዊዘርላንድ ባለስልጣናት ታግዶ ወደ ናይጄሪያ ተመልሷል፤
- ግለሰቡ በሥልጣን ዘመኑ በቢሊዮን የሚገመት ዶላር እንደ መዘበረ መረጃዎች ያሳያሉ፤
- ሀብቱ የተመለሰበት አግባብ ሀገሪቱ በ1998 ያቋቋመችው Special police investigation እና ያወጣችው domestic and recovery ህግ እንዲሁም ከፕሬዚዳንቱ ስልጣን መልቀቅ በኃላ የመጡ መሪዎች (General Abubeker እና የፕሬዚዳንት Obasanjo) ትጋትና ቁርጠኝነት ወሳኝ ነበር፤
- **ሌላው ናጄሪያ** ባለሥልጣናት **በውጪ ሀገር የባንክ አካውንት እንዳይከፍቱ** ክልከላ ጥላለች፤

# ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ለማጋለጥ ሚና ያላቸው አካላት



## ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማጋለጥ ተግዳሮቶች

- በሀገር ደረጃ በቴክኖሎጅ የታገዘ የመረጃ ቋት አለመዘርጋቱ፤
- ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማጋለጥ እና ህጋዊ እርምጃ በሚወስዱ አካላት መካከል ያለው ቅንጅት ዝቅተኛ መሆን፤
- ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን የሚያጋልጡ ዜጎች/ጠቋሚዎች ቁጥር አነስተኛ መሆን፡
- ለጠቋሚዎች የሚሰጥ ከለላ በቂ እና ወቅታዊ አለመሆን፣
- ለጠቋሚዎች የሚሰጥ ማበረታቻ ተግባራዊ አለመሆን፣

# ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማጋለጥ ተግዳሮቶች…የቀጠለ

- ሀብት በማስመለስ ዙሪያ በመንግስታት መካከል የጋራ ትብብር በሚፈለገው ደረጃ አለመዳበር
- የተዘረፈ ሀብት እንዳይሸሽ ወይም ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስመለስ ወጥነት ያለው የአፈፃፀም ማዕቀፍ አለመኖር፤
- አገራዊ እና አህጉራዊ ስምምነቶችን በሚፈለገው ደረጃ ተግባራዊ አለማድረግ፤
- የተቋማት ትብብር፤ ቅንጅት እና የመረጃ ልውውጥ ስርዓት አነስተኛ መሆን፤

# በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- የተጀመረውን የኦንላይን የሀብት ምዝገባ ተግባር በጥራትም በፍጥንትም ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፣
- የተጀመረውን የሀብት መረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥ(Verification) ወቅታዊ ምዝገባ ማካሄድን፣ የተመዘገበ መረጃ ትክክለኛነት ማረጋጋጥን፣ አላግባብ መበልፀግን እና የጥቅም ግጭትን ማጋለጥ በሚያስችል ሁኔታ አጠናክሮ መተግበር፣
- ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዘው የተገኙ ወይም አላግባብ ለመበልፀግ በሚሞክሩ አካላት ላይ አስተማሪ የሆነ የህግ ቅጣት ቢጣል፤

# በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ...የቀጠለ

- ጠቋሚዎች ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን እንዲያጋልጡ በሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጅ 668/2002 የተደነገገውን 25 በመቶ(ከሚወረስ ሀብት) ማበረታቻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- ዜጎች ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን በማጋለጣቸው በራሳቸው እና በቤተሰቦቻቸው ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የሚያደርግ ግልፅ ሥርዓት መዘርጋት እና ፈጣን ከለላ እና ጥበቃ እንዲኖር ማድረግ፣ አሠራሩ ላይም ለመላው ዜጋ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መስራት፤



# እናመሰግናለን!!

## Gadda ge!!

## Thank you!!